ሰዎች በአዛንና በመጀመሪያ ሰልፍ ያለውን ምንዳ ቢያውቁና እርሱንም እጣ ካልተጣጣሉ በቀር የማያገኙት ቢሆን ኖሮ እጣ ይጣጣሉ ነበር።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል፦ "ሰዎች በአዛንና በመጀመሪያ ሰልፍ ያለውን ምንዳ ቢያውቁና እርሱንም እጣ ካልተጣጣሉ
በቀር የማያገኙት ቢሆን ኖሮ እጣ ይጣጣሉ ነበር። (ወደ መስጊድ) ማልዶ የመሄድን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ ለርሱ ይሽቀዳደሙ ነበር። የዒሻና ሱብሒን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እየዳኹም ቢሆን ይመጡ ነበር።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሰዎች በአዛንና በመጀመሪያ ሰልፍ የሚገኘውን ደረጃ፣ መልካምና በረከት ቢያውቁ ኖሮና ከዚያም ለመቀደምና ቅድሚያ ለማግኘት ማነው የሚገባው ለሚለው እጣ መጣጣል ቢጠበቅባቸው ኖሮ እጣ ይጣጣሉ ነበር። ወደ ሶላት በመጀመሪያ ወቅት ቀድሞ የመሄድንም ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ ይሽቀዳደሙ ነበር። ወደ ዒሻ ሶላትና ወደ ፈጅር ሶላት መስጂድ የመምጣት ምንዳ መጠኑን ቢያውቁ ኖሮና ወደ መስጂድ መምጣት ቀላል ባይሆንላቸው ኖሮ ህፃን ልጅ እየዳኸ እንደሚመጣው በጉልበታቸው እየዳኹም ይመጡ ነበር አሉ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/65735